# የለውጥ ፕሮግራሞች ፕሮጀክት ጥናትና ትግበራ የስራ ሂደት

## ሀ. የሂደቱ ተልዕኮ

የማስፈፀም አቅም ክፍተትን በየጊዜው እየለየ የታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት ፣ ለጥናት ግብዓት የሚሆኑ ሃሳቦችን በማቅረብ ጥናቶችን በማስጠናት አዳዲስ አሰራሮችን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ሥልጠናና የምክር አገልግሎት በማሰጠት የማቴሪያል፣ የቴክኒክ ድጋፍ እና የአፈፃፀም የቅርብ ክትትል ድጋፍ በማድረግ የለውጥ ፕሮግራሞችን መከታተልና መገምገም ማስተግበር ነው ፡፡

## ለ. የሂደቱ ዓላማ፣ ዝርዝር ዓላማ፣ የሚጠበቁ ውጤቶች እና በጥረት የሚደረሱ ግቦች፣

### 1. ዓላማ

የዚህ የሥራ ሂደት ዋናው ዓላማ ጉታች፣ ነባር እና ውጤት አልባ የሆኑ አሰራሮችንና አደረጃጀቶችን በአዳዲስ አሰራሮች በመተካትና በማስተግበር የተለወጡ ወይም የማስፈፀም አቅማቸው የተገነባ ተቋማትን መፍጠር ነው ፡፡

### 2. ዝርዝር ዓላማዎች :-

- ☆ የማስፈፀም አቅም ችግሮችን ወይም ክፍተቶችን በየጊዜው በመለየት ለጥናት የሚሆኑ ግብዓቶችን በማስተላለፍ ክፍተት እንዲሞላ ማድረግ
- ☆ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተገልጋይ ተኮር የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት፣
- ☆ የመንግሥትን ገንዘብ እና ንብረት አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓት ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተጠያቂነት የሰፈነበት ማድረግ ፤
- ☆ መልካም ሥነ ምግባር ያለውና ብልሹ አሠራርን የማይቀበል ሲቪል ሰርቪስ መፍጠር
- ☆ በጥናት የተገኙትን አዳዲስ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን ለመተግበር የሚያስችል ሥልጠና በማሰጠትና የማስፈፀም አቅምን በዘላቂነት በመገንባት መልካም አስተዳደር ማስፈን
- ☆ ትግበራውን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት አቅም መገንባት

3. <u>ከሥራ ሂደቱ የሚጠበቁ ውጤቶች</u> <u>/Desired Out Come/</u>

- ☆ የዞኑ የመንግሥት ተቋማት በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች መሠረት ተለውጠው ደንበኛ ተኮር፣ ቀልጣፋ፣ ግልፅ፣ ወጪና ጊዜ ቆጣቢ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ አቅማቸው እንዲገነባ ይደረጋል ።
- ☆ ለመንግሥት ተቋማት በሥልጠና በአዳዲስ የጥናት ውጤቶች፣ በልምድ ልውውጥና በትግበራ ወቅት በሚሰጥ ቴክኒካል ድጋፍ ተቋማዊ የማስፈፀም አቅማቸው እንዲገነባ ይደረጋል ።

4. <u>በጥረት ተደራሽ ግቦች</u> <u>/ Stretch Objectives/</u>

- ☆ ትግበራ፣ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ይወስድ የነበረውን 175 ቀናት በ 72 ቀናት እንዲከናወን ማድረግ
- ☆ በትግበራው የአገልግሎት አሰጣጥ የደንበኞችን እርካታ ከ 26% ወደ 100% ማሳደግ
- ☆ ለትግበራ የተዘጋጀውን አንድ የለውጥ ፕሮጀክት ለትግበራ በተመረጡ የመንግሥት መ/ቤቶች 100% ተደራሽ በማድረግ እንደ አሰራር ስርዓት መትከል

ሐ. <u>የተገልጋዮችና የባለድርሻ አካላት ፍላጐት</u>

| *ተ/ቁ* | *ተገልጋዩና ባለ ድርሻ አካላት (Customers)* | *ፍላጐት (Needs & Expectations)* | *የሚጋራቸው ፍላጐት* (Common Themes) |
|---|---|---|---|
| 1 | የዞን፣ የከተማ አስተዳደር የወረዳ የመንግሥት ተቋማት እና የገጠር ቀበሌ አስተዳደር | በጥናት ውጤት ላይ የተመሠረተ ችግር ፈቺ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል በቀላል አቀራረብ የተዘጋጀ የሪፎርም ማስፈፀሚያ ሰነድ ይፈልጋሉ ። | ☆ ጥራቱን የጠበቀ የማስፈፀም አቅም /የተስተካከለ አሠራር፣ አደረጃጀትና አመለካከቱ የተቃኘና ብቃት ያለው ሲቪል ሰርቫንት/ የተገነባላቸው የመንግሥት ተቋማት<br>☆ ውጤታማ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ የሆነ የሪፎርም ትግበራ እና ሥራ ላይ |
| | | በጥናት የተመሠረተ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ የሚውል ውጤታማ የሆነ የማስፈፀም አቅም /የተስተካከለ አሰራርና አደረጃጀትና አመለካከቱ የተቃኘ ሲቪል ሰርቫንት/ እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ ። | |
| | | በየሴክተር መ/ቤቶች እየተሰራባቸው ከሚገኙ ልዩ ልዩ መመሪያዎችና ደንቦች በጥናት እየተፈተሹ ጉታች የሆኑ አሰራሮች በቀጣይነት እንዲሻሻሉ ይፈልጋሉ ። | |
| | | ወቅታዊ፣ በቂ ጊዜ የተመደበለት በፍላጐት ላይ የተመሠረተ ጥራት ያለው አጫጭር የሪፎርም ሥልጠናና የምክር አገልግሎት ። | |
| | | በቂ ዕውቀትና ክህሎት ማስጨበጥ በሚችሉ ባለሙያዎች የሚሰጥ ድጋፋዊ ክትትል | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥጥር ላይ ያልተመሠረተ ቴክኒካል እገዛን ማዕከል ያደረገ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ | የዋለ የተስተካከለ አሰራርና አደረጃጀት<br>☆ አቅማቸው ተገንብቶ ዕቅዳቸውን በብቃት ማሳካት የቻሉና የተለወጡ የመንግሥት ተቋማት |
| | | የለውጥ ፕሮግራሙ በሁሉም የመንግሥት ተቋማት ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ስኬታማ በሆነ መልኩ ተደራሽ በማድረግ አቅማቸው የተገነባና የተለወጡ የመንግሥት ተቋማት እንዲኖሩ ይፈለጋል ። | |
| | | የለውጥ ፕሮግራሙ በአንድ ቅኝትና አመለካከት ቅደም ተከተል ወጥቶለት ተግባራዊ እንዲሆን የመደገፍ የማስተባበርና የመምራት ሥራ እንዲሰራ ይፈለጋሉ ። | |
| 2 | ዞንና የወረዳ መንግሥት | የሲቪል ሰርቪሱን አመለካከት የማነጽ አቅሙን የማጐልበትና የማብቃት ሥራ እንዲሰራ ይፈልጋሉ ። | |
| | | የወረዳና የቀበሌ አስተዳደር መዋቅር ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይፈልጋሉ ። | |
| 3 | ለጋሽና አበዳሪ ድርጅት | በፈቀዱት በጀት፣ በሰጡት ብድር ወይም ዕርዳታ የሚጠበቀው ሥራ መሠራቱንና ውጤት መገኘቱን ማየት ይፈልጋሉ ። | |

## መ. <u>የሂደቱ ዋና ዋና ተግባራት (Milestones)</u>

☆ የአፈፃፀም ክፍተት መለየት

☆ የጥናት ስራውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

☆ የሥልጠና ፍላጐት መለየት

☆ የትግበራ ድጋፍና ክትትል ማድረግ

☆ የፋይዳ ግምገማ ማካሄድ

## ሠ. <u>አገልግሎት ለማግኘት ተገልጋዮች ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች</u>

☆ የሥራ ሂደቱን አገልግሎት ማግኘት የሚችሉ ተቋማት በተጠናቀቁ ጥናቶች ላይ ሥልጠና ለማግኘት፡-

- ➡ የ BPR ጥናት ሰርቶ ሙሉ ትግበራ ያከናወነ ተቋም

☆ **የትግበራ ድጋፍ ለማግኘት ፡-**

- ➡ በጥናቱ ውጤት ላይ ሥልጠናውን መውሰድ
- ➡ በትግበራ ዕቅድ ላይ በጋራ ተወያይቶ የአፈፃፀም ስምምነት ውል ከትግበራ ሂደት ጋር መፈራረም ፣
- ➡ በውሉ መሠረት ወደ ትግበራው መግባት ፣

➡ የአፈፃፀም ሂደትን በውል ስምምነቱ መሠረት ለአቅም ግንባታ ሴክተር ሪፖርት ማቅረብ

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራም